# የሳዑዲ አረቢያ መንግስት ሰነድ አልባ ዜጎች እንዲወጡ አሳሰበ



የሳዑዲ አረቢያ መንግስት ያለስራ እና የመኖሪያ ፍቃድ በአገሪቱ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የተለያዩ አገር ዜጎች እንዲወጡ አሳሰበ፡፡ በርካታ ሰነድ አልባ ዜጎቻቸው በአገሪቱ ከሚኖሩ የምህረት አዋጁ ከሚመለከታቸው አገራት አምባሳደሮች ጋር ሪያድ ውስጥ የተወያዩት የሳዑዲ መንግስት የአዋጁ አስፈጻሚ አባላት፣ በቀሪ ጥቂት ቀናት ውስጥ ኢትዮጵያውያን ዜጎች አገሪቱን ለቀው እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋል፡፡

ይህንኑ ተላልፈው በአዋጁ ከተገደበው ጊዜ በኋላ በአገሪቱ የሚቆዩ ዜጎች በድንጋጌው የተቀመጠውን ህጋዊ እርምጃ ለመቀበል የግል ሃላፊነት መውሰድ እንደሚኖርባቸው የሳዑዲ አረቢያ መንግስት አሳስቧል፡፡

በስብሰባው የተገኙት በሳዑዲ አረቢያ የኢፌዲሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር አሚን አብዱልቃድር የሳዑዲ አረቢያ መንግስት የኢትዮጵያን መንግስት ጥያቄ በመቀበል የእፎይታ ጊዜውን ለማራዘም በመወሰኑ አመስግነው፣ የመውጫ ቪዛ ወስደው በተለያዩ ምክንያቶች ወደ አገራቸው ያልተመለሱ ዜጎቻችን የቪዛው ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ለማድረግ ኤምባሲው ቅስቀሳ እያካሄደ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የሳዑዲ አረቢያ መንግስት የሰጠው የእፎይታ ጊዜ ሊጠናቀቅ አራት ቀናት የቀሩት ሲሆን ዜጎቻችን አሁንም ይህንን እድል ባለመጠቀማቸው ለችግር እንዳይዳረጉ የኢፌዲሪ መንግስት ያሳስባል፡፡

*የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር*

*ቃልአቀባይ ጽ/ቤት*

*ሀምሌ 12 ቀን 2009 ዓ.ም*